Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Standard level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau moyen – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel medio – Prueba 1

Wednesday 4 May 2016 (afternoon)
Mercredi 4 mai 2016 (après-midi)
Miércoles 4 de mayo de 2016 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

**Instructions to candidates**

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a guided literary analysis on one passage only. In your answer you must address both of the guiding questions provided.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

**Instructions destinées aux candidats**

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez une analyse littéraire dirigée d'un seul des passages. Les deux questions d'orientation fournies doivent être traitées dans votre réponse.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est de **[20 points]**.

**Instrucciones para los alumnos**

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un análisis literario guiado sobre un solo pasaje. Debe abordar las dos preguntas de orientación en su respuesta.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.

2216 – 0011

4 pages/páginas

© International Baccalaureate Organization 2016

International Baccalaureate
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

https://xtremepape.rs/

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ ትንታኔ ስጥ:: ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርብሀል::

**1.**

ከዘመናት መሃል በሰባ ሰባቱ
እኛና ተፈጥሮ ቀልባችን ሲፋቱ
የፍጥረትን ነዲድ ጭሱን እየማገ
ሰማዩ ደንብሮ ሆዱ ተሸለገ
አፈር ትቢያ ወርሶት ጭጋግ አለገገ::
ነበልባል ዘነበ ወላፈን ነፈሰ
ዘራሰብ ከአፈር ጋር በእሳት ተጠበሰ::
አሞራ አራዊቱ በድን እየጎተቱ
ስጋ አጥንት ሲለቅሙ
ሰይጣን አጋንንቱ ቅዱስ መላዕክቱ
ለእኛ ለእኛ እያሉ በነፍስ ተሻሙ::

እኔም ተቸግሬ
በወርሃ ሰኔ አንጀቴን አስሬ
የዘራሁትን ዘር በነመጋል ቡሬ
ከጣልሁበት ማሳ ባጣው አፈር ጭሬ
ለእግዜር ለተፈጥሮ እንዲህ አልኩ አምርሬ::
«ምነው ሰማያቱ
ህልቆ መሳፍርቱ
በእኛ ላይ ዘመቱ በእኛ ላይ ዶለቱ!!
ምነው በሰንበቱ
ቁራሽ ከሌማቱ
ሽሮ ከወጪቱ አለመገኘቱ?!
ምነው ህፃናቱ
እንስሳ አራዊቱ
እንደሳር ደረቁ በጠኔ ተመቱ!
በአላቱን ሳልሽር አርብ ሮብን ፆሜ
በሰንበት በንግሱ ለቅዳሴ ቆሜ
ያወረድሁት እንባስ ያ ኪራራይሶ
የኔን ለቅሶ ያህል
ማዝነብ አይችልም ወይ ወደእኔ መልሶ?
እባክህ ፍረደኝ እባክህ ፍረደን
ካፈር ሰው አብቅለህ እህል አትካደን!»
ብለው ተንሰቅስቁ የእግዜር ግን ትዕግስቱ
ከሰው ከእንስሳቱ
ከእኔም ህይወት በላይ ሆነና ስፋቱ
በዝምታ አለፈኝ
ከሰማያት ሆኖ እያየኝ በሩቁ
እኔም እጅ ሰጠሁ ባለስቃይ ትጥቁ
የሰቆቃው ጌታ አነቀኝ ጭራቁ::

https://xtremepape.rs/

ያኔ እንደሰማዩ ራቀኝ አንጀቴ
መተንፈስ ታከተኝ ተረታ ጉልበቴ
ደምስሬ ደረቀ አካሌ ታወከ
ሆድ እቃዩ ታልቦ ጀርባዬን ታከከ።

ሰይጣን አጋንንቱ ቅዱስ መላእክቱ
ዙሪያዩን ከበቡኝ መጡ ወደራሴ
ለእኛ ለእኛ እያሉ ሊሻሙ በነፍሴ።
ይብላኝ ለተረኛ ለእኔ ባልንጀራ
የኔውስ ተዳርሷል ስቃዩ ሊያባራ
ነፍሴ ለመናፍስት ስጋዩ ላሞራ።

ይርጋ ገላው፣ የተራሮች ጩኸት፣ (1998)።

(a) በግጥሙ ስለቀረበው መልእክት ያገኘሽው ግንዛቤ ምንድነው?

(b) ፀሀፊው የቃላት ድግግሞሽ ቴክኒክ በመጠቀም የግጥሙን መልእክት እንዴት እንዳጎለበተ አስረዳ።



https://xtremepape.rs/

**2.**

ከመሄዴ አስራ አምስት ቀን በፊት አጎቴ ከከተማ ወደ እኛ ቤት መለስ ቀለስ ማለት አብዝቶ ነበር:: መጥቶ በሄደ ቁጥር ወላጆቼ ያስጨነቃቸውን ጉዳይ ለማወቅ እጅጉን ጓጓሁ:: በተለይ እናቴ ጭብጥ ኩርምት ስትል መክረሟን ስላየሁ ጉዳዩን ማወቅ አጓጓኝ:: አጎቴ የገጠር ኑሮን እርም ብሎ መሬቱን የግሚስ ሰጥቶ ከተማ ከገባ አራት ዓመት እንደዘለለው ሰምቻለሁ:: ከተማ ገብቶ ምን እንደሚሰራ የማውቀው ነገር የለም:: ነገር ግን “ከተማ ይግደለኝ! ተገጠር ሀብታም ገበሬ የከተማ ሸቃይ ይሻላል!” ማለትን ያዘወትራል::

ለሶስተኛ ጊዜ እንደመጣ ጆሮዬን ቀስሬ ከወላጆቼ ጋር የሚያወሩትን አዳምጥ ነበር:: የሚወያዩት እኔን ወደ ደብረ ብርሃን ትሂድ አትሂድ እያሉ መሆኑን ፍንጭ አገኘሁ:: በጣም ደነገጥኩ፣ ከቤተሰቦቼ መለዬትን እንዴት ልችለው ነው እያልኩ መጨነቅ ጀመርኩ:: የአባቴ የሁለቴ ታናሽ የሆነው አጎቴ ከተማ በመግባቴ የሚገጥሙኝን ዕድሎች ለወላጆቼ ያወራል::…

“ወንድም ጋሼ ሙት ሸንኮሬን እኮ አለማወቅህ ነው:: እንኳን የኛን ያገሯን ሰው ልዥ ቀርቶ ከየገጠሩ የማንንም ልዥ ሰብስባ አስተምራ አሳድጋ ትልቅ ቦታ ያደረሰች ነች:: ቅርንጫፉ በዛና ዝምድናችንን በውል አለማወአችን እንጂ ታባታችን ጋር የተቋጥሮ ዝምድና እንዳለን ነግራኛለች:: ለካስ ወንድም ጋሼ ያልወለደ ሰው እንቅልፍ የለውም::! አሁን እድሜዋም ሲገፋ የማስተምራትና ሀብት ንብረቴን በቁሜ የማወርሳት የዘመድ ልዥ ታላመጣህልኝ ብላ መግቢያ መውጫ አሳጣችኝ:: መቼስ ይሄን ሲሳይ የናቴ ልዥ አንተ እያለህ ለባዳ አሳልፌ አልሰጥም ብዬ ነው እንደ ውሃ ቀጂ የምመላለሰው…” አለ ወደ አባቴ እያዬ፣

አጎቴ የሚናገርላቸውንና የገጠር ልጆችን አስተምረው ለወግ ማዕረግ የሚያበቁትን ደግ ሴት ለማየት ናፈቅሁ:: እኚህ ደግ ሴት እኔንም ከገጠር በተሻለ የከተማ ትምህርት ቤት አስተምረው ትልቅ ቦታ ሲያደርሱኝ ታየኝ:: ወላጆቼም እኚህ የተባረኩ ሴት ላይ እንዳይጨክኑ በልቤ መማፀን ያዝኩ::

“እውነት ነው መሽታ… አንተም ለኛ ብለህ ነው:: እኔም እኮ የተፈታተንኩህ ተአምስት ወንዶች መሃል የተፈጠረች አንድ ልጌን እንዴት ታጠገቤ ላርአት ብዬ እንጂ የክፋትም አዶል::”

“አይ ወንድም ጋሼ ሴት ልዥህ ታንተ ጋር ዘላለም ትኖር ይመስልሃል? አሁን የአገራችን ልማድ ጠፍቶህ ነው:: አጎጠጎጤ ማውጣት ስትጀምር አይደል ለጋብቻ ስጡን በሚል ሽማግሌ ሲግተለተል የሚውለው:: አይሆንምም ብትል አንዱ ጥጋበኛ ጠልፎ ጉድ ይሰራሃል:: ያኔ ትምርቷም ተስተጓጉሎ፣ ተገጠር ኑሮ ታትወጣ እዚሁ እንደታተረች ትኑር?” ሲል ሰውነቴን ሰቀጠጠኝ::

“ተው ተው መሽታ! የሰይጣን ጆሮ ይደፈን::… እሱስ እኔም ሁሌ እንቅልፍ እንደነሳኝ ነው:: አይ መሽታ ምነው ኩፉኛ ፈተንከኝ!… ተተፈጠርኩ እስተ ዛሬ ስደርስ እጅግ የፈተነኝ ጉዳይ ቢኖር ዛሬ ይዘህብኝ የመጣኸው ጉዳይ ነው::… ወይ ፈተና!… እንግዲህ እንደፈቀደው አንተን ወንድሜንም ተማስቀይም ልጌቷም ፈጣሪ ያዘዘላትን አዱኛ ተምንገፋ በጄ ብለናል…” አለ አባቴ::

እናቴ ግን እንደተከዘች ተቀምጣለች::አጎቴም ሃሳቧን አልጠየቃትም:: አባዬም ሃሳብ እንድትሰጥ አልጋበዛትም:: እሷም ተቃውሞ ይሁን መስማማት ባይገባኝም አቀርቅራ መሬት በስንጥር ከመቆርቆር ውጪ ቃል አልተነፈሰችም::

ግርማ ነሲቡ፣ *ታጋቾቹ* (2007)::

(a) በቅንጭብ ጽሁፉ የከተማና የገጠር ህይወት በንጽጽር እንዴት ቀረቡ?

(b) ፀሀፊው ምልልስን በመጠቀም የግጥሙን መልእክት እንዴት እንዳጎለበተ አስረዳ::

https://xtremepape.rs/